የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fourth Year No. 31
ADDIS ABABA 18 February 2012

***ማውጫ***

የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አዋጅ

***CONTENTS***

**Yekatit 12 Hospital Medical College Proclamation**

## አዋጅ ቁጥር ፴፩/፪ሺ፬
## የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ አዋጅ

በሽታን በመከላከል ላይ የተመሠረተዉን የሀገራችን የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የህብረተሰቡ የጤና ዋነኛ ችግሮች የሆኑትን ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እንዲያስችል ተቋማዊ አቅምንና ሙያዊ ብቃትን ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ ያለውን የከፍተኛ ጤና ባለሙያዎችን በተለይም ጠቅላላ ሐኪሞችንና እስፔሻሊስት ሐኪሞች እጥረትን ለመፍታት የንድፈ-ሀሳብና ተግባር ተኮር ስልጠናን በማቀናጀት በሆስፒታል ማዕከልነት ስልጠናንና የጤና አገልግሎትን አዋህዶ በቂ ችሎታና ጥራት ያላቸዉን ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች የሚያመርት የጤና ሳይንስ ሥልጠና ማዕከልን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭/፪ እና በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬(፩) (ሀ) መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## Proclamation No. 31/2011
## Yekatit 12 Hospital Medical College Estabishment Proclamation

WHEREAS, it is found necessary to build institutional capacity and professional strength to ensure effective implementation of the national health policy that emphasises on tackling of the main health problems of our society, the spread of communicable and non communicable diseases, through preventive measures;

WHEREAS, it is required to establish medical training center under the city Government of Addis Ababa to train higher and medium level health professionals through applying a new method of training that sufficiently combines theoretical training with practical application in amalgamation with hospital health service delivery so that to give enduring solution to the shortage of specialized and general practitioner medical professionals that has been seriously constraining the effective implementation of the national health policy;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 5(2) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009 as well as Article 14(1)(a) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No.361/2003 the City Council of Addis Ababa has issued this proclamation as follows;

12
31

***ክፍል አንድ***
***ጠቅላላ ድንጋጌዎች***

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፪ሺ፬» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. «ቢሮ እና የቢሮ ኃላፊ» ማለት በቅደም ተከተል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እና የጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፤

፫. «አዋጅ» ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ ነው፤

፬. «ፕሮቮስት» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሾመ የኮሌጁ የበላይ ኃላፊ ነው፤

፭. «የአካዳሚ ሠራተኛ» ማለት በኮሌጁ ውስጥ በማስተማርና በምርምር ሥራዎች ላይ የተሰማራ ነው፤

፮. «የህክምና ሠራተኛ» ማለት በኮሌጁ ሆስፒታል ዉስጥ በጤና ሙያ የሚያገለግል ሠራተኛ ነዉ፤

፯. «የአስተዳደር ሠራተኛ» ማለት በኮሌጁ ወስጥ የአስተዳደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሠራተኛ ነው፤

፰. «ቦርድ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል የሜዲካል ኮሌጅ የአመራር ቦርድ ነው፤

፱. «ኮሌጅ» ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ነው፡፡

**፫.መቋቋም**

፩. የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ ኮሌጁ እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ኖሮት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፤

፪. በአዋጁ ለትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የኮሌጁ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል:

፫. አግባብነት ያላቸው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ድንጋጌዎች ከኮሌጁ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

***Part One***
***General Provisions***

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the «Yekatit 12 Hospital Medical College Establishment Proclamation No. 31/2011».

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this proclamation;

1. "Government" means the Addis Ababa City Government;
2. "Bureau and Bureau head" means the Health Bureau and Head of the Health Bureau of the City Government of Addis Ababa, respectively;
3. "Proclamation" means the Higher Education Proclamation No. 650/2009;
4. "Provost" means the chief administrator of the College, who is appointed in accordance with this proclamation;
5. "Academic Staff" means member of the college engaged in a capacity of teaching and research;
6. "Medical staff" means member of the college engaged in medical service thereof;
7. "Administrative staff" means member of the college engaged in rendering administrative service;
8. "Board" means the governing board of the college established in accordance with this proclamation;
9. "College" means the Yekatit 12 Hospital Medical College established in accordance with this proclamation.

**3. Establishment**

1. Yekatit 12 Hospital Medical College (here after called the college) is hereby established by this proclamation having legal personality;
2. The colledge shall be accountable to the Bureau;
3. Relevant provisions of the Higher Education Proclamation shall be applicable to the college;

**፬.ዓላማ**

ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ንድፈ ሃሳብንና ተግባራዊ ስልጠናን ያዋሃደ የትምህርት ሥርዓትን በመዘርጋት በተለያዩ መርሀ-ግብሮች የጤና ባለሙያነት ትምህርት ስልጠና በመስጠት ብቁና መልካም ሥነ-ምግባርን የተላበሱ የጤና ባለሙያዎችን ማፍራት፣

፪. በህብረተሰቡ የጤና ችግር ላይ የተመረኮዘና ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር የተጣጣመ የጤና አገልግሎት መስጠት፣

፫. በጤናው ዘርፍ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት፣ ጥናትና ምርምር በማድረግ የህብረተሰቡን የጤና ችግር መቅረፍ፡፡

**፭. የሥራ ነጻነትና ተጠያቂነት**

ኮሌጁ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች በአግባቡ ለማሣካት የሚያስችል የሥራ ነፃነት ኖሮት በተገቢዉ ኃላፊነትና ሕግ ተጠያቂነት መሠረት ይተዳደራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

**፮. አደረጃጀት**

ኮሌጁ፡-

፩.ቦርድ

፪.ሴኔት

፫.ፕሮቮስትና ምክትል ፕሮቮስቶች

፬.የአስተዳደር ጉባኤ

፭.የአካዳሚክ ኮሚሽን እና

፮.አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፯. የኮሌጁ ስልጣንና ተግባር**

ኮሌጁ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ይሰጣል፣

፪. የጤና አገልግሎት ክፍሎችና ልዩ ልዩ ማዕከሎችን ይከፍታል፣ያስተዳድራል፣

፫. ፕሮግራሞች፣ ፋካልቲዎች፣ ልዩ የትምህርት ክፍሎችንና የትምህርትና ምርምር ማዕከሎችን በመክፈት የመጀመሪያ ዲግሪና የድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞችን በመዘርጋት ይተገብራል፣ በሥርዓቱ ይመራል፣

**4. Objectives**

The college shall have the following objectives;

1. Produce highly qualified and competent health professionals through applying new method of training that sufficiently combines theoretical and practical training;
2. Provide health service focusing on the alleviation of health problems of the society that are highly prevalent at the grass root level;
3. Abolish the society's health problem by giving them education and training and by also conducting health problem solving researches.

**5. Independence and Accountability of the College**

The college shall be autonomously organized and independently function in a manner that would enable it to achieve its objectives stipulated in this proclamation.

## *Part Two*
## *Organizational structure, power and function*

**6. Organizational structure**

The college shall have;

a. Board
b. Senate
c. Provost and vice provosts
d. Managing council
e. Academic commissions and;
f. Other relevant staff members

**7. Power and function of the college**

The college shall have the following power and functions፡-

1. Provide quality and, well standardized health service to the public;
2. Establish and run various health service providing units and centres;
3. Implement and apply graduate and post graduate programs through organizing programme units, faculties, departments, education and research centres that are structured under its system;

፬. የትምህርት ማስረጃ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሰዎች የአካዳሚ ሹመትና የሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል፣

፭. ቅድሚያ በሚሰጣቸው የጤና ጉዳዮች ላይ ችግር ፈቺ ምርምሮችን ያካሂዳል፣

፮. ከመንግስትና የግል የትምህርት ተቋማት ለልምምድ የሚመጡትን ተማሪዎች የአገልግሎት ዋጋ በህግ መሠረት ያስከፍላል፣

፯. የህብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ የጤና አገልግሎት ክፍያዎችን በማጥናት ለቢሮው ያቀርባል፣ በከተማዉ አስተዳደር ካቢኔ ሲወሰንም ሥራ ላይ ያውላል፣

፰. የታካሚዎችን ቅብብሎሽ ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥና የጤና ድርጅቶች አስተዳደር መመሪያ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል፣

፱. ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የኮሌጁ ሠራተኞችና ተማሪዎች የጤና አገልግሎት ያገኛሉ፣

፲. ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶች ሲምፖዚየሞችን ያዘጋጃል፣

፲፩. የህክምናና የጤና ትምህርትና ስልጠና መፅሔቶችንና ጋዜጦችን ያሳትማል ያሰራጫል፣

፲፪. በሀገር ውስጥና በውጭ ሃገሮች ካሉ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፣

፲፫. የዕዉቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ አቅጣጫዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል።

## ክፍል ሶስት

## የኮሌጅ አመራር አካላት አመሠራረትና ስልጣንና ተግባር

**፰. የቦርዱ አመሠራረትና ተጠሪነት**

፩. የየካቲት ፲፪ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ የሥራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኃላ «ቦርዱ» እየተባለ የሚጠራው በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

፪. የቦርዱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።

**፱. ስለ ቦርዱ አባላት**

፩. የቦርዱ አባላት ብዛት ፕሮቮስቱን ጨምሮ ዘጠኝ ይሆናሉ፣

፪. ፕሮቮስቱን ሣይጨምር የቦርዱ አባላትና ሰብሳቢ በቢሮው ኃላፊ ቀርበው በከተማዉ ከንቲባ ይሰየማሉ፣

4. Confer academic certificates diplomas, degrees and others related credentials as well as awards academic titles and medals for those who have made commendable contribution;

5. Undertake problem solving researches on prioritized health streams;

6. Serve as a venue for apprentice from both private and public medical colleges with imposition of fees in accordance with the law;

7. Prepare proposals to determine fees for medical service, in consideration with the financial capacity of the community and submit it to the Health Bureau and implement same upon approval by Cabinet of the City Government;

8. Design applicable system in order to facilitate medical service delivery that targets patients who pass through the regularly applied referral procedure;

9. Make medical service available for the students and staffs of the college in accordance with directives of the board;

10. Organize seminars and workshops on issues that are pertinent for its mission;

11. Publish and disseminate medical and health teaching training jowrnals and newsle tters;

12. Establish relationship with domestic and foreign colleges of the same stream;

13. Design directions for knowledge and technology transfer; implement same.

## *Part Three*

## *Establishment, function and Acountability of the Governing bodies of the college*

**8. Establishment and Accountability of the Colledge**

1. The governing board of Yekatit 12 Hospital Medical Colledge (hereafter called the board) is hereby established by this proclamation;
2. Accountability of the boord shall be to the bureau.

**9. Members of the board**

1. The board shall have nine members including the provost;
2. Excluding the provost, all other members of the board shall be appointed by Mayor of the City;

፫. ለቦርድ አባልነት የሚቀርቡ ግለሰቦች በኃላፊነት ላይ ያሉ ወይም ሲያገለግሉ የነበሩ ወይም በማስተማርና በምርምር ሥራ እውቅና እና ልምድ ያላቸው በአጠቃላይ ለኮሌጁ አላማ መሣካት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፣

፬. የቦርዱ አባላት የቆይታ ጊዜ አምስት ዓመት ሆኖ አንድ አባል ለተጨማሪ አንድ ጊዜ ብቻ ሊሰየም ይችላል፣

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ሥር የተደነገገው እንዳለ ሆኖ የቦርዱ አባላት በጠቅላላ ወይም በተናጠል በሚፈፀሙት ስህተት ምክንያት የቆይታ ጊዜያቸው ሳያበቃ ከአባልነት ሊሰናበቱ ይችላሉ።

፲. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ፤ ሆኖም ሰብሳቢው አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ።

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የተገኙ እንደሆን ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፣

፫. የቦርዱ ውሣኔ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ሆኖ እኩል ድምፅ በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፣

፬. ከቦርዱ አባላት ውስጥ ፩/፫ኛ ከጠየቁ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣

፭. የስብሰባው አጀንዳ ከስብሰባው ዕለት አምስት ቀን አስቀድሞ ለቦርዱ አባላት መድረስ አለበት።

፲፩. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

፩. ኮሌጁን በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል

፪. ይህ አዋጅና ሌሎች አስፈላጊ ህጐች በኮሌጁ ውስጥ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣

፫. የኮሌጁን ዕቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃጀት፣ የአስተዳደርና አሠራር ሥርዓት፣ የውስጥ ደንብና የአካዳሚክ ኘሮግራሞችን በተመለከተ የሚቀርቡትን ሐሣቦች መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፬. የኮሌጅን ኘሮቮስት የሚሆነውን ሰው በመምረጥ እንዲሾም ለቢሮው ኃላፊ ያቀርባል፣



3. The nominees for the membership of the board shall be highly qualified individual serving or used to serve as academicians in the intuitions of higher learning and earned commendable reputation for their academic excellencies and believed to give viable leadership and make the demanded contribution for the success of the colledge;

4. The tenure of the board shall be five years. However, any one of them can be reappointed for only one additional term;

5. With out prejudice to sub article 4 of this article, the members of the board collectively as well as separately shall be accountable for any wrong doing they commit.

**10. Meeting procedure of the board**

1. The board shall meet once a month, however the chair person may call an urgent meeting if it deems necessary;
2. It shall constitute a quorum when ever half of the members are present;
3. Decisions shall be passed by majority vote. When votes are equal, the decision that the chair person supports shall be the decision of the board;
4. If it is requested by ¾ of the members the chair person shall call an urgent meeting;
5. The agenda of the meeting shall have to be deliverd to each member five days prior to the meeting.

**11. Power and function of the board**

The board shall have the following powers and functions;

1. Oversight and coordinate the college as a supreme governing body;
2. Ensure proper application of this proclamation and other regulations and directives that it issues;
3. Discuss and approves the annual plan, the budget and prioritize the activities of the college as well as regularly scrutinize reports on the various activities;
4. Nominate a person who should be appointed as a provost of the college and presents to the bureau;

፮. የኮሌጁ ፕሮቮስት በሚያቀርበው ሐሣብ ላይ በመመርኮዝ ምክትል ፕሮቮስቶችንና የአካዳሚክስ ኃላፊዎችን እንዲሁም ሌሎች የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላት የሚታጩበትን፣ የሚሰየምበትን ወይም የሚመደቡበትንና የሚመረጡበትን መስፈርት በሚመለከት መመሪያ ያወጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፯. ምክትል ፕሮቮስቶች የሥራ ድክመት ካሣዩ ወይም ከፍተኛ ጥፋት ከፈፀሙ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፣

፰. የኮሌጁ ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ሲቀርብለት ምርምሮ ያረጋግጣል፣ በሚመለከተው አካል ከፀደቀ በኋላ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፱. የኮሌጁ ገቢ የሚሰበሰብበትን ሥርዓት እና ወጪውም በበጀት ዕቅድ መሠረት መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፲. በአስተዳደሩ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ሕግ ላይ በመመሥረት የአካዳሚክ፣ የህክምና እና የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር፣ዕድገት፣ ዲስፕሊንና ደሞዝ ሌሎች ጥቅማቅጥሞች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፲፩. የኮሌጁን የሥራና በጀት አፈፃፀም ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል፣

፲፪. ኮሌጁ በሚሰጣቸው ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ ከቀረበ በማጣራት የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፣

፲፫. የቀረቡለትን የኮሌጁን የሥራ አፈፃፀም በዕቅዱ መሠረት ይገመግማል፣

፲፬.የቦርዱን የውስጥ አሠራር እና የአባላት ስነምግባር በሚመለከት የውስጥ የመተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣

፲፭.በሴኔቱ የሚቀርቡለትን የፕሮፌሰርነት ማዕረግ በመመርመር ያፀድቃል፣

፲፮.በኮሌጁ ፕሮቮስት የሚቀርቡለትን የልዩ ልዩ ክፍያ ፕሮፖዛሎች በማየት ይወስናል፣

፲፯.የትርፍ ሠዓት ክፍያ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ የኮሌጁን አቅም ባገናዘበ መልኩ አግባብነት ባለው ሕግ በተወሰነው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

6. Set modalities and establish procedures for appointment of the vice provosts and issue directives for the effect;

7. Take corrective measure when the vice provosts show weakness in their discharge of responsibilities and commit mistakes;

8. Confirm and approve strategic plans, annual reports on the performances and proper utilization of budget after thoroughly discussing and submits to the concerning bodies and commands their implementation when the concerning body ratifies;

9. Follow up the revenue collecting system of the college and confirm whether the expenditure commensurate with the annual budget;

10. Follow up the procedures of employing academic, medical and administrative staffs of the college whether the application is based on the relevant laws and regulations of the government that are set to administer civil servant;

11. Reports submit performance reports and budgets to the bureau;

12. Give final decisions on complaints raised against any the decisions of the college after investigating;

13. It shall evaluates the over all performances of the colledge;

14. Issue directives to establish the modus operndi of the board itself and ethical codes for its members;

15. Confer professorships submitted to it by the Senate;

16. Determine various payment proposals that the college provost submits for decision;

17. Follow up the proper effect and fairness of payments Determined for benefits and honorarium for extra-hour works;

፲፰. ለቦርድ አባላት የሚውሉ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች በቢሮው ከፀደቁ በኋላ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

**፲፪. የሴኔት አባላት**

የኮሌጁ ሴኔት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩.የኮሌጁ ፕሮቮስት ......... ሰብሳቢ

፪. ምክትል ፕሮቮስቶች ................አባል

፫. የፕሮግራም ኃላፊዎች......... አባል

፬. የቤተመፃህፍትና ኢንፎርሜሽን ክፍል ኃላፊ .......................................አባል

፭. ሬጅስትራር ............ አባል

፮. ሁለት የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካይ....አባል

፯. አንድ የተማሪዎች ተወካይ ... አባል

**፲፫. የሴኔቱ ስልጣንና ተግባራት**

ሴኔቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. የኮሌጁ የትምህርት ፕሮግራምና ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፪. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በመመስረት የተማሪዎች አስተዳደር ሁኔታ፤ የኮሌጁን የትምህርት ጉዳዮች፤ የትምህርት ክፍሎች ኃላፊዎች አመራረጥ፤ ቅጥር፤ ደረጃና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ስነምግባርና የአካዳሚክ ሠራተኞች ደሞዝ በተመለከተ የውስጥ መመሪያ ያወጣል፣

፫. የአካዳሚክና የህክምና ሠራተኞችን ቅጥር ያፀድቃል፤ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሐሣብ ያቀርባል፣

፬. የተማሪዎች ቅበላ፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰን፣ የዲሲፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል፣ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚነሱትን ቅሬታዎች መርምሮ ይወስናል፣

፭. የፈተና እና የደረጃ አሰጣጥ አጠቃላይ አቅጣጫ ይወስናል፣

፮. የሴት ተማሪዎች ቅበላና የሚደረጉ ድጋፎች ሥርዓት ይዘረጋል፣

18. Ensure the applicability of allowances and other benefits for board members after being set by the bureau.

**12. Members of the Senate**

The senate of the college shall have the following members;

1. Provost of the college…..............chairman
2. Vice provosts of the college …member
3. Heads of programmes………member
4. Chief librarian and head of information department…member
5. The registrar…..................member
6. Two representatives of the academic staff……member
7. A representative of the students…member

**13. Power and function of the Senate**

The senate shall have the following powers and functions;

1. Cause implementation of academic programs and systems of the college;
2. Issue directives regarding student administration, academic issues, nomination and election of department heads, hiring of staffs, promotion and dismissal, benefits and allowances and ethical codes and ensure their proper implementation;
3. Approves hiring of academic and medical staffs, and prepare and submit proposal to confer professorship;
4. Set criteria for admission of students, determination of academic standards, dicipilinary matters and graduation, and examine and decide on appeals relating thereof;
5. Sets general guide lines to determine examination and academic standards;
6. Place a system for affirmative actions targeting female students in order to fill the gender imbalance between female and male students;

፰. በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የተማሪዎች ቅበላ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ምረቃውንም ያፀድቃል፣

፱. የራሱን የስብሰባ እና የአሠራር ሥርዓት ያወጣል፣

፲. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ የራሱን ስልጣንና ተግባራት ለኮሌጁ አካላት በቋሚነትና በጊዜያዊነት ለማቋቋሙት ኮሚቴዎች ሊያስተላልፍ ይችላል፣

፲፩. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

### ፲፬. የፕሮቮስትና ምክትል ፕሮቮስቶች አሿሿምና ከሹመት ስለሚነሱበት ሁኔታ

፩. የኮሌጁ ፕሮቮስት የሚሆነውን ሰው በ ቢሮው አቅራቢነት በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ይሾማል፣

፪. የኮሌጁ ምክትል ፕሮቮስቶች በቦርዱ አቅራቢነት በቢሮዉ ይሾማሉ፣

፫. የፕሮቮስቱ የሥራ ዘመን ፭ ዓመት ሲሆን የምክትል ፕሮቮስቶች ፬ ዓመት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰዉ ለአንድ ጊዜ ብቻ በድጋሚ ሊሾም ይችላል፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወይም በሌላ ምክንያት ፕሮቮስቱ ወይም ምክትል ፕሮቮስቶች በጠቅላላ ወይም በተናጠል ከኃላፊነታቸዉ ሊሰናበቱ ይችላሉ፣

፭. ቢሮው ከኃላፊነቱ በተነሳው ተሿሚ ምትክ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ሌላ እንዲሾም/ሌሎች እንዲሾሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### ፲፭. የፕሮቮስቱ ስልጣንና ተግባር

የኮሌጁ ፕሮቮስት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. ኮሌጁን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪. የኮሌጁን አካላትና ማህበረሰብ የከፍተኛ. ትምህርት ዓላማና እሴቶች ማክበራቸውን ያረጋግጣል፣



8. Place a system to admit students for post-graduate programs;
9. Establish procedures for its meetings and modus operandi;
10. With out prejudice to the provisions of this article, it may temporarily or permanently delegate some of its function to the appropriate bodies of the college;
11. Perform other functions assigned to it by the board.

### 14. Appointment and dismissal of the provost and vice provosts

1. The provost of the college shall be appointed by the Mayor of the city up on the recommendation by the bureau;
2. The vice-provosts of the college shall be appointed by the bureau up on the recommendation of the board.
3. The tenure of the provost shall be only 5 years while the vice provosts shall serve for four years. However, the tenure of the provost can be extended for one more addtional term;
4. Without prejudice to sub article 3 of this Articles, the provost and the vice provosts may be collectively and separately dismissed due to any liability incurred to the college and weakness in the discharge of their responsibility;
5. The bureau shall cause appointment of new provost or vice provosts within a period not more than a month.

### 15. Power and function of the provost

The provost of the college shall have the following responsibilities.

1. Give leadership to the college as a chief administrator;
2. Confirm whether the educational objectives and values of the college are properly observed and respected by the college community;

፫. ኮሌጁ አስተዳደሩ በሚፈልገው መጠን ጥራትና ብቃት ያለዉ የሰው ኃይል መፍጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

፬. የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የጤና አገልግሎት ሥራን የሚያበረታታ የኮሌጁን የትምህርትና የጤና ማህበረሰብ ይፈጥራል፣ በቀጣይነት ይገነባል፣

፭.በኮሌጁ የሚካሄዱ የምክርና ምርመራ ሥራዎች አገሪቷና አስተዳደሩ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፮. ኮሌጁ ዓላማውን ለማሳካት ከፌዴራል፣ከሌሎች ክልል አካላት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እንዲሁም ከአቻ የዉጪ አገር ተቋማት ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፣

፯. የሰው ኃይል አመራርና አስተዳደር ሥርዓት፣ በአደረጃጀቱና በአሠራሩ የኮሌጁን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል እንዲሆን ያደርጋል፣

፰. የአካዳሚክስ ኃላፊዎችና የአካዳሚክ ኮሚሽን አካላት አሰያየም ሥርዓት በማዘጋጀት በቦርዱ ከፀደቀ በኂላ ሥራ ላይ ይውላል፣

፱. በትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ በተቋማዊ ነፃነትና ተጠያቂነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና በወጪ ቆጣቢነት መርሆዎች ላይ በመመስረት የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትን ለአካዳሚክ ኮሚሽኑና ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፣

፲. የቅጥር ኃላፊነት ቦታዎች በውድድር የሚያዙ መሆኑንና ከኃላፊነት መነሳትም በሥራ አፈፃፀም ግምገማ፤ በዲሲኘሊን ጉዳይ እና በአገልግሎት ዘመን ማብቃት ብቻ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ያረጋግጣል።ስህተት በተፈጠረበት ቦታ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፣

፲፩.የኮሌጁ ገቢ.ና ወጪ በመንግስት ፋይናንስ ሕግ መሠረት መከናወናቸውንና መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

3. Introduce a system whereby the college produces human resource compatible with the demands of the City Government in quantity, quality and competence;

4. Create and build continuously educational and medical community whose mission is to facilitate teaching learning process and health service delivery in the college;

5. Confirms the research undertakings and consultancy activities of the college are in conformity with national priorities;

6. Foster relation of the college with governmental and non governmental bodies in the Federal and Regional levels as well with foreign counterpart institutions in a manner that can help the college to achieve its objectives;

7. Ensure the compatibility of human resource organization and administration of the college in line with its desire to accomplish its mission;

8. Design proper mechanism for nomination of members for academic commission and submits to the board and implement it after the approval by the board;

9. Persuade both the board and the academic commission on the ways of making the education and research activities relevant, quality and result oriented, cost effective as well as operations are based on the principles of institutional independence, transparency and accountability and seeks their approval to make organizations of departments on line with these;

10. Confirms whether employments being merit based, promotions and dismissals are effected based on pr oper performance evaluations, disciplinary grounds and end of the tenure;

11. Confirm whether the revenue and expenditure management of the college are in accordance with the relevant regulations and laws of the government;

፲፪. የአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባና ሌሎች ከአስተዳደር ጋር የተያያዙ ስብሰባዎች በቂ ዝግጅት ተደርጐ በወቅቱ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

፲፫. በኮሌጁ ውስጥና በሦስተኛ ወገን መሀከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የኮሌጁን ተልዕኮ ጥቅም ለማሳካት በሚያስችል መልክ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈታ ያደርጋል፣

፲፬.የኮሌጁ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ግንኙነቶች ትክክለኛ በሆነ የመረጃ ሥርዓት መመዝገባቸውን መረጃዎች በደንብ መጠበቃቸውንና ለሚመለከተው አካል መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣

፲፭.የኮሌጁን የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፲፮.የቦርዱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያቀርባል፣

፲፯.ኮሌጁ ከሦስተኛ ወገን ጋር ለሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሌጁን ይወክላል፣

፲፰.የኮሌጁን የባንክ ሂሣብ በህግ መሠረት እንዲከፈት ያደርጋል፣ ያንቀሳቅሳል፣

፲፱.የውጪ ሀገር ጉዞ የኮሌጁን ጥቅምና በዕቅድ የተያዘ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፳.በሥራ ላይ መገኘት በማይችልበት ጊዜ ከምክትል ፕሮቮስቶች ውስጥ አንዱን መወከል ይችላል።

፲፮.ስለ ምክትል ፕሮቮስቶች

ኮሌጁ አንድ የአካዳሚ እና ምርምር ምክትል ፕሮቮስት፣ አንድ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሮቮስት እንዲሁም አንድ የጤና አገልግሎት ዘርፍ ይኖረዋል።

፲፯. የአካዳሚክና ምርምር ም/ፕሮቦስት ተግባርና ኃላፊነት

፩. የኮሌጁን አጠቃላይ አካዳሚያዊና የምርምር ሥራዎችን በሚመለከት የውሳኔ ሀሳቦችን አዘጋጅቶ ለፕሮቦስቱ ያቀርባል፣

፪. የኮሌጁን አካዳሚክ ካላንደር አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቅለትም አፈፃፀሙን ይመራል፣

፫. የየትምህርት ክፍሎች ኃላፊዎች በትምህርት ክፍሎች መምህራን እንዲመረጡ ያደርጋል፣

12. Make academic and other administrative meetings of the colledge are conducted in timely basis after having proper preparations;

13. Resolve disputes arise within the colledge and with the third party legally and peacefully in a manner that helps to advance the accomplishment of the colledge's mission;

14. Confirms proper documentation, storage, preservation and dissemination of information about all basic activities and relations of the colledge;

15. Prepare annual budget of the college and implements it when it gets approval;

16. Disseminate reports of the board to the concerning bodies;

17. Represents the colledge in relation with the third parties;

18. Open bank accounts for the colledge in accordance with applicable laws;

19. Confirm the effects of foreign trips are whether only to the benefits of the colledge and implemented in accordance with predetermined plans;

20. Assign one of vice provosts to represent him in his absence.

**16. Functions and responsibilities of the vice provosts.**

The colledge shall have academic and research vice provost administrative and development viceprovost and medical service vice provost.

**17. Functions and responsibilities of the academic and research vice provost**

1. Prepares proposals regarding academic and research works of the college and submits to the provost;
2. Prepares the academic calendar of the college and coordinates its application;
3. Supervise the election of department heads by their respective staffs;

፬. የምርምር ሀሳቦች ተግቢነትን በመወሰን ይመርጣል። የመረጣቸዉንም በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለፕሮቦስቱ ያቀርባል።

፭. የጸደቁ የምርምር ሥራዎች እንዲታቀዱና ከታቀዱም አፈጻጸማቸዉን ያስተባብራል።

፮. በፕሮቮስቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

## ፲፰.የአስተዳደርና ልማት ም/ፕሮቮስት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ኮሌጁን ለማሳደግና አገልግሎቱን አድማስ ለማስፋት የታለሙ ስራዎችን በበላይነት ይመራል።

፪. የኮሌጁን አስተዳደረዊና የሰዉ ኃይል ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል። ለኮሌጁ አስተዳርና ልማት ዘርፎች የሚያስፈልገዉን የሰዉ ሓይል ብዛት በተመለከተ የዉሳኔ ሀሳብ አዘጋጁቶ ያቀርባል። ሲጸድቅም በህግ አግባብ መሰረት እንዲሟሉም ያደርጋል።

፫. የኮሌጁን ዓሜታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለፖርቮስቱ ዉሳኔ ያቀርባል።

፬. ኮሌጁን አካዳሚያዊ ተግባሮችን ለማሳካት የሚያግዙ ድጋፍ ሰጪ ስራዎችን በበላይነት ያስተባብራል።

፭. ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ አቅርቦቶችና ለህክምና አገልግሎት የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል።

፮. የኮሌጁን ደህንነት እንዲጠበቅ ሀብትና ንበረት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲዉል የሚያስችሉ ስራዎችን ይሰራል።

፯. የኮሌጁ አካዳሚያዊ ሠራተኞችን በተመለከተ ደረጃ እድገትና ሙያዊ ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ የወጡ መመሪያዋችንና ወሳኔዎችን ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።

፰. በፕሮቮስቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

## ፲፱. የህክምና አገልግሎት ዘርፍ ም/ፕሮቦስት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ለኮሌጁ የህክምና አሰጣጥ ዘርፍ የሚያስፈልገዉን የአግልግሎት ዓይነት ደረጃና ስፋት እንዲሁም የሚያስፈልገዉን የሰዉ ሓይል መጠን በተመለከተ ዝርዝር ሀሳቦችን አዘጋጅቶ ያቀርባል።

4. Make decisions on research ideas based on their relevance and submit proposals for their application to the provost;
5. Incorporate the approved research ideas in the annual research plan and coordinate their implementation;
6. Performs other duties assigned to him by the provost.

## 18. Functions and responsibitities of Administrative and Development vice provost

1. Coordinate all activities intended to develop and expand the scope of the college's service;
2. Give leadership in matters related to human resource of the college and prepares proposals regarding the requiring number of employees for the development activities of the college and submits for decision by the provost;
3. Prepare the annual comprehensive working plan of the college and submits to the provost;
4. Coordinate all facilitative activities for the proper undertaking of academic works of the college;
5. Be responsible for all necessary supplies that the teaching-learning process and students, accommodations require;
6. Be responsible for the security of the college and protection of all properties under its jurisdiction;
7. Be responsible for the implementation of all benefits and entitlements of academic and non academic staffs as per to their approval;
8. Perform other duties assigned to him by the provost.

## 19. Functions and responsibilities of Medical Service vice provost of the college

1. Prepare proposal about the kind of service and standard that Health service delivery of the College requires with the necessary amount of labour for decision;

፪.የፀደቁና ዉሳኔ ያገኙ ሀሳቦችችንም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫.የኮሌጁን አጠቃላይ የህክምና ዘርፍ ዕቅድን አዘጋጅቶ ለፖርቦስቱ ያቀርባል። ዕቅዱ የፀደቀ ሲሆንም አፈፃፀሙንም በበላይነት ይመራል፣

፬. የኮሌጁን የህክምና ዘርፍን ዕለታዊ እንቅስቃሴን በበላይነት ይመራል፣

፭. የኮሌጁ አካዳሚያዊ ሰራተኞ በህክምና አሰጣጥ ሥራ የሚሰማሩበትን ፕሮግራም ያዘጋጃል፣

፮. በኘሮቨስቱ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

**፳. የአስተዳደር ጉባኤ አባላት**

፩.የኮሌጁ ኘሮቮስት ...............ሰብሳቢ

፪.ምክትል ኘሮቮስቶች ........... አባል

፫.የተማሪዎች ዲን ............... አባል

፬.በኘሮቮስቱ የሚመረጡ ፫ ሰዎች...... አባል

**፳፩. የአስተዳደር ጉባኤ ስልጣንና ተግባር**

፩.በዋና ዋና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ኘሮቨስቱን ያማክራሉ፣

፪.በኮሌጁ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ይወያያሉ፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣

፫.የዕቅድ፣ በጀት፣ አደረጃጀትና የትምህርት ኘሮግራሞች መመሪያ፣ የትምህርት ክፍሎችን መደባለቅና መለያየት ረቂቅ ሐሣብና የአፈፀፃም ሪፖርት ላይ ይወያያሉ።

**፳፪. የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላት**

፩. የአካዳሚክና ምርምር ኘሮቮስት...ሰብሳቢ

፪.የትምህርትክፍል ኃላፊዎች..........አባል

፫.የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካይ......አባል

፬.አንድ የተማሪዎች ተወካይ ......አባል

፭.በኘሮቮስቱ የሚመረጡ ፫ ሰዎች ......አባል



2. Implement the decisions and approved proposals;
3. Prepare the annual plan of the hospital and submits to the provost as well as leads the implementation the approved plan;
4. Coordinate the routine works of the health service delivery of the college on a daily basis;
5. Schedule for the engagement of academic staffs in the health service delivery of the college;
6. Performs any related activities that are assigned to him by the provost.

**20. Members of the managing council of the college**

1. Provost of the college...............chairman
2. Vice provosts.....................member
3. Student dean ..........................member
4. Three persons selected by the provost......member

**21. Power and function of the managing council**

1. Advice the provost on major strategic issues ;
2. Discuss on the over all achievements of college and forward solutions for the identified problems;
3. Discuss on reports about budget utilization academic programs and proposals on the separation and merger of departments and study programs.

**22. Members of the academic commission**

The academcic commission of the college shall have the follwing members

1. Academic and Research vice provost ...chairman
2. Department Heads .........Member
3. Representatives of the academic staff...member
4. Representatives of the students......member
5. Three other persons nominated by the provost....... Member.

**፳፫. የአካዳሚክ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር**

፩. የአካዳሚክ ኮሚሽኑን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በጀት በማዘጋጀት ያስፀድቃል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፪. የትምህርት ሥርዓት ወይም የስልጠናና ትምህርት ማሻሻያ ዕቅድ በማዘጋጀት ለሴኔት ያቀርባል::

፫. በሴኔት መመሪያ መሠረት የትምህርትና የተማሪዎች ዲስፕሊን መስፈርት ይወሰናል፣

፬. ከትምህርት ጋር የተያያዙ የክብር ሽልማትና ዲግሪ እንዲሰጡ ለሴኔት ሐሣብ ያቀርባል፣

፭. በሴኔት መመሪያ መሠረት የሌክቸረር፤ ረዳት ሌክቸረር፤ ረዳት ምሩቃን እና የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲቀጠሩለት ብዛትና አይነቱን ለይቶ ያቀርባል አጣርቶም ይቀበላል፣

፮. የፕሮፌሰርነት ሹመት እንዲሰጥ ለሴኔቱ ሐሣብ ያቀርባል፣

፯. የስብሰባና የአሠራር ሥርዓት ያወጣል::

፰. የነፃ ትምህርት ዕድል፣ የሰባቲካል እና የምርምር እረፍት ያፀድቃል፣

፱. በሴኔቱና በፕሮቮስቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

**፳፬. የኮሌጁ የአካዳሚክ ሠራተኞች**

የኮሌጁ የአካዳሚክ ሠራተኞች ጊዜያቸውን ለሕክምና አገልግሎት፤ ለማስተማርና ለምርምር ሥራዎች ሚያውሉት ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወስናል::

**፳፭. የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት**

፩.ኮሌጁ በጤና ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውንና አግባብነት ባላቸዉ የተፈጥሮ ሣይንስመስኮች ተመርቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ እና በኮሌጁ የሚወሰኑትን መስፈርቶች የሚያሟሉትን ለቅድመ ምረቃ ትምህርት ይቀበላል፣

፪.የከፍተኛ ትምህርት ቅድመ ምረቃ ትምህርት ያጠናቀቁና በኮሌጁ የሚወሰኑትን መስፈርቶች የሚያሟሉትን ለድህረ ምረቃ ትምህርት ይቀበላል፣

**23. Power and functions of the academic commissions**

1. Prepare academic plans of the colledge and submits it for approval and follow up its implementation after its being approved;
2. Prepare plans for education system and other trainings by the colledge;
3. Code of conduct for students based on the directives of the senate;
4. Submits proposal about conferring of honorary academic titles and other awards and submits it to the senate;
5. Prepares proposals about the number of assistance lectures, lecturers, gradates and assistance graduates and other professionals that the work of the college requires;
6. Prepare and submit proposal about conferring of professorship;
7. Determines procedures for its meeting;
8. Approves scholarships abroad and sabbatical leaves;
9. Performs other undertakings given by the senate and the provost.

**24. Duties of the academic staffs**

The academic staffs of the college are duty bound to allot all their working time for academic and research works of the college.

**25. Students Admission criterias**

1. The college shall admits for its graduate programmes those who are holding first degree in health and natural sciences and currently at service in addition to fulfilling other requirements set by it;
2. The college shall admit those who have accomplished pre-graduate education and would be able to qualify its requirements;

፫. ለሴት ተማሪዎች ልዩ የቅበላ ሥርዓት ሊወስን ይችላል፣

፬. ኮሌጁ የሚቀበላቸው ተማሪዎች አግባብ ባለው ህግ የትምህርት የወጪ መጋራት ግዴታ የሚወጡ መሆን አለባቸው፣

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሌጁ የትምህርት ክፍያ በማስከፈል ሊያስተምር ይችላል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፮. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

የካቲት ፲፪ ሆስፒታል መብትና ግዴታዎችበዚህ አዋጅ መሰረት ለኮሌጁ ተላልፈዋል።

**፳፯. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች**

፩. የካቲት ፲፪ ሆስፒታልን በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፩ አንቀፅ ፭/፳፩/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፳፰. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፲ ቀን ፪ሺህ፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ
የካቲት ፲ቀን ፪ሺህ ፬

ኩማ ደመቅሳ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ



3. It may set separate requirements for admission of female students;
4. The admitted students should be able to express their willingness to share the expenses of their education based on cost sharing regulation of the government;
5. Without prejudice to sub article 4 of this article the college may admit students imposing education fees.

## Part Four

## *Miscellaneous Provisions*

**26. Transfer of rights and obligations**

The rights and obligations of Yekatit 12 Hospital are hereby transferred to the Yekatit 12 Hospital Medical College by this proclamation.

**27. Repealed and Inapplicable Laws**

1. Regarding Yekatit 12 Hospital Article 5(21) of the Addis Ababa City Government Executive and Municipality Service Organs Re-establishment Proclamation No. 15/2009 is hereby repealed by this proclamation;
2. Any proclamation, regulation, directive or customary practice inconsistent with matters provided for in this proclamation shall have no effect.

**28. Power to Issue Regulation**

The City Cabinet may issue regulation for the implementation of this proclamation.

**29. Effective Date**

This proclamation shall enter into force as of 18th date of February 2012.

**Done at Addis Ababa**
**This18th Day of February 2012**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**